ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አራት ምርጫዎች በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀትህ /ሽ ላይ በማጥቆር መልስ/ሽ

1. ስለ ፊዚካላዊ ቁስ አካላት እንቅስቃሴ የሚያጠና የፊዚክስ ቅርንጫፍ የቱ ነው
   A. አስትሮ ፊዚክስ B. ኒውክለር ፊዚክስ C. መካኒክስ D. ኦፕቲክስ
2. የብስክሌት ጎማ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በየትኛው እንቅስቃሴ አይነት ውስጥ ይመደባል?
   A. ኩርባዊ እንቅስቃሴ B.ክበባዊ እንቅስቃሴ C. እርግብግባዊ እንቅስቃሴ D. የቀጥተኛ መስመር እንቅስቃሴ
3. አንድ ባቡር 50 m/s ቋሚ ፍጥነት ቢጓዝ 2Km ርቀት ለመሸፈን ምን ያህል ጊዜ ይፈጅበታል ?
   A. 25s B. 100s C. 40s D. 52s
4. የሰበቃ ኃ ይልን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   A. የሰበቃ ሀይልን መቀነስ እንጂ ማጥፋት አይቻልም
   B. ቋሚ የሰበቃ ኃይል ከእንቅስቃሴያዊ የሰበቃ ኃይል ይበልጣል
   C. የእንቅስቃሴያዊ ሰበቃ መጣኝ ከቋሚ የሰበቃ መጣኝ ያንሳል
   D. በማንከባለል ፋንታ ማንሸራተት የሰበቃ ኃይልን ይቀንሳል።

5. 5m ከፍታ ካለው ፎቅ ላይ የተለቀቀ ኳስ በምን ያህል ፍጥነት መሬት ይደርሳል? ($g=10m/s^2$)
   A. 50m/s B. 15m/s C. 10m/s D. 5m/s

6. ከሚከተሉት ውስጥ የነኪ- ኃይል የሆነው የቱ ነው?

   A. የማግኔት ኃይል B.የሰበቃ ሀይል C.የመሬት ስበት ሀይል D.የኤሌክትሪክ ኃይል

7. $59^0$F የሆነ መጠነ ሙቀት በከልቪን ስኬል ስንት ይሆናል ?

   A. 288k B. 15k C. 258k D. 9k

8. ከሚከተሉት ውስጥ የባትሪ ወካይ የሆነው የቱ ነው?

   A. B. C. D.



9. ከሚከተሉት ውስጥ የመፈንቅል ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?

   A. መቀስ B. መዶሻ C. የጠርሙስ መክፈቻ D. በከራ

**NAFYAD SCHOOL**



10. ከሚከተሉት ውስት የስራ አሃድ ያልሆነው የቱ ነው?

A. J B. Kg $m^2$/s3 C. Nm D. Kg $m^2$/s2

11. ከሚከተሉት ውስጥ የፍዘት ህግ የሆነው የቱ ነው?

A. 1 ኛ የኒውተን የእንቅስቃሴ ህግ B. 3 ኛ የኒውተን የእንቅስቃሴ ህግ

C. 2 ኛ የኒውተን የእንቅስቃሴ ህግ D. ግብር እና አፀፋ ግብር

12. የግለት ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

A. የነገሮች መስፋፋት B. የሁነት ለውጥ C. በካሜራ ፎቶ ማንሳት D. ቡና ማፍላት

13. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. MA>1 ከሆነ ማሽኑ ኃይል አብዢ ይሆናል B.የሰበቃ ኃይል እንደሌላ ከታሰበ VR<MA ይሆናል

C. VR<1 ከሆነ ማሽኑ ቶሎታ አብዢ ይሆናል። D. MA=1 ከሆነ ጭነት እና እንቅስቃሴ ኃይል እኩል ይሆናሉ

13. በአንድ የኤሌክትሪክ አስተላላፊ ውስጥ 800mA ከረንት ለ 20s ያህል ካለፈ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚተላለፈው የሙል መጠን ስንት ይሆናል?

A. 160C B. 1600c C. 1.6C D. 16C

15. ከሚከተሉት ውስጥ መሰረታዊ ተሰፋሪ አካል የሆነው የቱ ነው?

A. ፍጥነት B. ርዝመት C. እፍጋት D. ኃይል

16. ከሚከተሉት ግራፎች ውስጥ የተመሳሳይ ፍጥነት እንቅስቃሴ የሚያሳየው የቱ ነው?

A.



B.



C.



D.


t t

17. መጠነ ሙቀቱ $30^0C$ በሆነ አየር ውስጥ የድምፅ ፍጥነት ስንት ይሆናል?(Vo=331 m/s) ተጠቀሙ

A. 361m/s B. 339m/s C. 349m/s D. 318 m/s

18. አንድ ብርቱካን ከምን ያህል ከፍታ ላይ ቢለቀቅ በ 3s ውስጥ መሬት መድረስ ይችላል?

A. 15M B. 40m C. 90m D. 45m

19. የኤሌክትሪክ ከረንት መለኪያ መሳሪያ የሆነው የቱ ነው?

A. አሜትር B. ቮልት ሜትር C. አምፒር D. ኦም ሜትር

20. ብቃቱ 80% የሆነ ማሽን የፍጥነት ሬሽዬው 4 ቢሆን የማሽኑ የመካኒካል ጥቅም ስንት ይሆናል?

A. 20 B. 3.2 C. 84 D. 240

21. ከሚከተሉት ውስጥ የማሽኖች ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው ?

A. ኃይልን ማብዛት B. ፍጥነት ማብዛት C. ጉልበት ማብዛት D. የኃይልን አቅጣጫ መቀየር

22. አንድ ካውያ 1Kw የሚል ፅሁፍ አለው። ይህን ካውያ ለ 5s ለመጠቀም ምን ያህል ጉልበት ያስፈልጋል?

A. 200J B. 5000J C. 500KJ D. 2000KJ

23. ከሚከተሉት ውስጥ መፍላትን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. በማንኛውም የፈሳሽ አካል ውስጥ ይከሰታል B.የቅዝቃዜ ውጤት ነው

C. በቁሱ ወለል ላይ ብቻ ይከሰታል D.በወለል ስፋት ላይ ይወሰናል

24. ድምፅ በፍጥነት የሚተላለፈው በየትኛው ሁነት ውስጥ ነው ?

A. ፈሳሽ B. ጋስ C. ውሃ D. ጠጣር

25. የከህሎት ልዩነቱ 80V ከሆነ ባትሪ ጋር የተያያዘ መስመር ውስጥ 160c ሙሎች በ 4s ውስጥ ቢተላለፍ የመስመሩ

ሙግደት ስንት ይሆናል?

A. 120 Ω B.40Ω C. 2Ω D.30Ω

26. ከሚከተሉት ውስት ሙል አልባ ቅንጣጢት የሆነው የቱ ነው ?

A. ኒውትሮን B. ኤሌክትሮን C. ፕሮቶን D. ኒውክለስ

27. ከሚከተሉት ውስጥ የኃይል ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

A. የነገሮች ቅርጽ መቀየር B. እንቅስቃሴን ማስጀመር C. ፍጥነትን መጨመር D.መጠነ ቁስ መቀየር

28. መጠነ ቁስ 20kg የሆነን አካል በ $5m/s^2$ ሽምጠጣ ለማሽምጠጥ ምን ያህል ኃይል ያስፈልጋል?

A. 25N B. 4N C. 100N D. 15N

29. ክብደቱ በመሬት ላይ 100N የሆነ አካል ጨረቃ ላይ ስንት ይሆናል? (g መሬት $=10m/s^2$) ( g ጨረቃ= $1.63\ m/s^2$)

ተጠቀሙ )

A. 16.3N B. 163N C. 1000N D. 1.63N

30. $^1/5$ ሰዓት ስንት ሴኮንድ ይሆናል?

A. 540s B. 12s C. 300s D. 720s

31. አንድ መኪና ከእረፍት ላይ በመነሳት በ 4s ውስጥ 240m ርቀት ወደ ሰሜን ቢጓዝ በዚህ ጊዜ ማለቂያ ላይ የመኪና

ሽምጠጣ ምን ያህል ይሆናል?

A. $15\ m/s^2$ B. $12m/s^2$ C. $24m/s^2$ D. $480\ m/s^2$

32. የሞጋጆች ሙግደት የተገላቢጦሽ ምዝነት ያለው ከየትኛው ጋር ነው?

A. መጠነ ሙቀት B. ርዝመት C. የተሰራበት ቁስ አካል አይነት D. የአግድም ገፅታ ስፋት

33. የኃይል ስፍር የሆነው የቱ ነው?

A/ [$MLT^2$] C/ [ $MLT^{-2}$]

B/ [ $ML^2T$] D/ [ $ML^{-2}T$]

34. በጋስና በፈሳሽ ውስጥ የሚፈፀም የግለት መተላለፊያ መንገድ የሆነው የቱ ነው?

A. ንክኪ B. ኮንቬክሽን C. ራዴሽን D. ጨረራ

35. የአንድ ሳጥን መቀመጫ ስፋት 6$m^2$ ነው።የዚህ ሳጥን ክብደት 360N ቢሆን መቀመጫው ላይ የሚፈጠረው ግፊት ስንት ይሆናል?

A. 8640pa B. 144pa C. 2160pa D. 60pa

36. በሁለት መስታወቶች መሀከል የሚፈጠረው የምስል ብዛት 4 ቢሆን በሁለቱም መስታወቶች መሀከል ሊፈጠር የሚችለው ዘዌ ስንት ነው?

A. $72^0$ B. $60^0$

C. $89^0$ D. $90^0$

- ቀጥሎ ያለውን ምስል በመመልከት 37ኛ እና 38ኛ ጥያቄዎችን ስሩ።




37. የመስመሩ ጠቅላላ ሙግደት ስንት ይሆናል?

A.8Ω B.2Ω C.9Ω D.1.5Ω

38. የመስመሩ ጠቅላላ ከረንት ስንት ይሆናል?

A.18A B.8A C.9A D.48A

39. የአንድ ካሬ ስፋት 144$m^2$ ቢሆን የጎኑ ርዝመት ስንት ይሆናል?

A. 36m B.16m C.9m D.12m

40. ከሚከተሉት ውስጥ የፈሳሾችን ግፊት የሚወስነው የቱ ነው?

A. ፈሳሹን የያዘው እቃ ስፋት B. የፈሳሹ መጠነ ሙቀት C.የፈሳሹ ጥልቀት D. ፈሳሹን የያዘው እቃ ቅርፅ

41. 2000g መጠነ ቁስ ያለውን አሉሚኒየም መጠን ሙቀቱን ከ $150^0$c ወደ $200^0$c ከፍ ለማድረግ የሚያስፈልገው የግለት

መጠን ምን ያህል ነው?(CAL=900J/$kg^0$C)

A. 90KJ B. 9KJ C.900KJ D. 9000J

42. ከሚከተሉት ውስጥ የመካኒካል ጉልበትን ወደ ኤሌክትሪክ ጉልበት የሚቀይር መሳሪያ የሆነው የቱ ነው?

A. ትራንስፎርመር B. ጄኔሬተር C. የኤሌክትሪክ ሞተር D. ባትሪ ድንጋይ

43. የአትሞስፌር ግፊት መለኪያ መሳሪያ የሆነው የቱ ነው ?

A. ቴርሞ ሜትር B.ኃይድሮ ሜትር C.ኃይድሮሊክ ፕሬስ D. ባሮ ሜትር

44. መጠነ ቁሱ 240kg የሆነ ሳጥን 4m ርዝመት፣ 3m ወርድ እና 5m ከፍታ ቢኖረው እፍጋቱ ስንት ይሆናል?

A. 6 $kg/m^3$ B. 12 $kg/m^3$ C. 4$kg/m^3$ D. 7 $kg/m^3$

45. ቀጥሎ ባለው ምስል ላይ የፅብረቃ ዘዌው ስንት ይሆናል?



45$^0$



A. 48$^0$ B. 42$^0$ C. 60$^0$ D.90$^0$